# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 116 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአምስተርዳም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ባዘጋጁት በዓል ላይ ሁከት ለመፍጠር የጠነሰሰው ሴራ ከሸፈ

በሆላንድ ዋና ከተማ አስምተርዳም በኢትዮጵያውያን ስደተኞች በተዘጋጀ በአል ላይ የወያኔ ቅጥረኞች ሁከት ለመፍጠር ያደረጉት ሙከራ በዝግጅቱ ታዳሚዎች እንደከሸፈ ለዝግጅት ክፍላችን ከስፍራው የደረሰ ዘገባ አሳይቷል።

ከሐምሌ 22 እስከ ሐምሌ 24 በአምስተርዳም የተካሄደው 8ኛው አመታዊ የኢትዮጵያዊያን-አውሮፓውያን የስፖርትና የባህል ፌስቲቫል በብዙ ሸህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና አውሮጳውያን በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል።

ወያኔ በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያውያን ተቋማትን ሰርስሮ በመግባት ለመከፋፈል እና ለማዳከም በያዘው እቅድ መሰረት ይህንን በአል ለመቆጣጠር ሞክሮ እንዳልተሳካለት ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት አገዛዙ ዝግጅቱን ለማወክ በመወሰን በአሉ ከመጀመሩ አንድ ቀን በፊት ከአዲስ አበባ ወደ አምስተርዳም ጥቂት ቅጥረኞችን ማጓጓዙ ታውቋል።

ከነዚህም ሰዎች ውስጥ አቶ ተኪኤ የተባለው ግለሰብ የዘረኛውን አምባገነን መለስ ዜናዊን ምስል የያዘ ከነቴራ ለብሶ ወደ በአሉ ስፍራ በመምጣት ሊቀሰቅስ የሞከረው ሁከት በታዳሚው አርቆ አሳቢነት ሊሳካ አልቻለም። ይሁን እንጂ፥ ቤልጂየም በሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ የደህንነት ሰዎች ታጅቦ የመጣው ተንኳሽ በማን አለብኝነት የበአሉን አስተባባሪዎች እና ሌሎች ግለሰቦች ማጥቃት ጀመረ። በዚህም ወቅት ጸቡን ለማብረድ የመጡ ሰዎችን ሳይቀር ማጥቃት መጀመሩ ያናደዳቸው ሰዎች በመረባረብ ጥቃት እንደፈጸሙበት ለማወቅ ተችሏል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጠና የፈጠረው ድብርት እንደተስፋፋ ነው፤ የሰሞኑ ሰለባዎች የዩኒቨርሲቲ ሰቃዮች መሆናቸው ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንዲቀበሉ ለማድረግ ባለው እቅድ መሰረት ሰሞኑን የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሰቃዮችን ያለ ፈቃዳቸው ሲሰብክ መቆየቱ ታውቋል።

አገዛዙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረ አንድ አመለካከት እንዲኖራቸው እና ተቃውሞ እንዲያቆሙ የማድረግ እቅድ እንዳለው ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ እራሱ መናገሩን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። በዚህም መሰረት ከመምህራን አንስቶ እስከ ወጣቶች እና የመንግስት ኦዲተሮች፤ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት ሁሉ ስልተና ሲሰጣቸው እንደቆየ ዘግበናል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ መሰረት፣ የዚህ ሳምንቱ ተረኞች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ምሩቃን ናቸው። እነዚህ ምሩቃን በውጤታቸው ምክንያት በተለያዩ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የኢትዮጵያን የደን ሽፋን በሶስት እጥፍ ጨምሬያለሁ ማለቱን የአገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ባለሙያዎች “የማይመስል ነገር” አሉት

የወያኔ አገዛዝ ባለፉት አስር አመታት ውስጥ የአገሪቱን የደን ሽፋን በሶስት እጥፍ ጨምሬያለሁ በማለት ያወጣውን ሪፖርት የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ባለሙያዎች “እውነትነት የጎደለው እና ጨቅላ” እንዳሉት አፍሪካጂት የተባለ የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል።

በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የግብርና ሚኒስቴር በዚህ ወር ባወጣው ሪፖርት የአገሪቱ የደን ሽፋን ባለፉት አስር አመታት ውስጥ ከሶስት ፐርሰት ወደ ዘጠኝ ፐርሰት ከፍ ብሏል ማለቱ ይታወሳል። የሚኒስቴር ቢሮው በነዚህ አመታት፣ በተለይም የሚሊኒየሙን በአል አስመልክቶ የተካሄደው የዛፍ ተከላ ዘመቻ ለእድገቱ ምክንያት ነው ብሏል።

አቶ ሚሊዮን በላይ የተባሉ እና በተፈጥሮ ጥበቃ ዘርፍ የሚሰሩ ግለሰብ ለአፍሪካጂት በሰጡት ቃል፥ ዛፍ መትከል ብቻ የደን ሽፋንን እንደማይጨምር ገልጸዋል። አቶ ሚሊዮን ከተተከሉት ዛፎች ውስጥ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

**ግዜ** ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከፍተኛ ትርፋማነት በታወጀ ማግስት በወደፊት እጣው ላይ ጥያቄ ተቀሰቀሰ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ ትርፋማ ከሆኑ አየር መንገዶች አንዱ ነው በተባለ ማግስት አንዳንድ የተቋሙ ሰራተኞች በወደፊት እጣው ላይ ጥያቄ እያነሱ ነው።

ናዝሬት ዳት ካም የተባለው የመረጃ ድረ-ገጽ “ኤር ትራንስፖርት ወርልድ” የሚባለውን ጋዜጣ ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአለም 16ኛ፣ ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛው ትርፋማ አየር መንገድ ነው። እስካሁን ባለው መረጃ፣ አየር መንገዱ 127.7 ሚሊዮን ዶላር ማትረፉን እና ባለፈው የፈረንጆች አመት 3 ሚሊዮን ሰዎችን ማጓጓዙን ጠቅሷል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ እና በአለማቀፍ ደረጃ በርካታ ሽልማቶችን የተቀበለ እንደሆነም ይታወቃል።

ይሁን እንጂ አንዳንድ የተቋሙ ሰራተኞች የድጅርቱን የወደፊት እጣ በሚመለከት ስጋት እንዳለባቸው መግለጽ ጀምረዋል። ድርጅቱን በመወከል በውጭ አገር ተቀምጠው እንዳሉ የገለጹ አንድ ግለሰብ ለግንቦት 7 ድምጽ ራድዮ ዝግጅት ክፍል በላኩት የኢ-ሜይል መልከት፣ ባለፈው አመት የተቋሙ ስራ አስኪያጅ አቶ ግርማ ዋቄ በፓርላማ የተናገሩትን በማስታወስ እሳቸው እና አንዳንድ የሚያውቋቸው ሰራተኞች የኢትዮጵያ ኩራት ለሆነው ለዚህ አንጋፋ ድርጅት እንደሚሰጉ ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በሺዎች የሚቆጠሩ የ ወረዳ መቀመጫዎችን እየሞላ ነው ተባለ

በ2000 አመተ ምህረቱ ህገ-ወጥ የማሟያ ምርጫ ተመርጠዋል በሚል በአዲስ የተለያዩ የቀበሌና የወረዳ አስተዳደራዊ መቀመጫዎችን የተረከቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያለ ምርጫ በተሰበሰቡ አዳዲስ ሹመኞች እየተተኩ መሆኑን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ አስታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከመዲናይቱ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ እንዳስታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በነዚህ ሰዎች ምትክ ለተሾሙ 2000 ሰዎች ስልጠናን እየሰጠ ነው። አዲሶቹ ሹመኞች በ2000 አመተ ምህረቱ ማሟያ ምርጫ ተመርጠዋል ተብለው፤ ነገር ግን የወያኔ አገዛዝ በሚፈልገው መጠን ለገዢው ፓርቲ ታማኝ ሆነው ያልተገኙትን የሚተኩ እንደሆኑም ለማወቅ ተችሏል።

በ2000 አመተ ምህረት ወያኔ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ እንዳይሳተፉ በማድረግ ብቻውን የተወዳደረበትን ህገ-ወጥ ምርጫ ማካሄዱ ይታወቃል። ቀድሞዉኑ ምርጫው ህገ-ወጥ መሆኑ ሳያንሰው፣ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የሃሰት ምርጫ ማካሄዱንም ወዲያ ብሎ ሰዎችን በቀጥታ መሾም መጀመሩ ገዢው ፓርቲ በአሁኑ ሰዓት ዴሞክራሲያዊነትን ማስመሰል ተስኖታል የሚሉ ድምጾችን አቋም አጠናክሯል። በግንቦት 15፣ 2002ቱ የምርጫ ተውኔት ማግስት፣ በርካታ የውጭና የአገር ውስጥ የፖለቲካ ተንታኞች ኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ አገር መሆኗን መናገራቸው ይታወሳል።

## በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የሚደርሰው ግፍ ቀጥሏል፤ በደቡብ አፍሪካ ሶስት ኢትዮጵያውያን በጩቤ ተወግተው መቁሰላቸው ተዘገበ

የተሻለ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ፍለጋ ወደ ውጭ በሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰው እንግልት ቀጥሎ በዚህ ሳምንት በደቡብ አፍሪካ ሶስት ኢትዮጵያውያን በጩቤ ተወግተው መጎዳታቸው ተዘግቧል። “ፍሮም ዘ አልድ” የተባለ የደቡብ አፍሪካ የዜና ድረ-ገጽ እንደዘገበው፣ የሶስቱ ኢትዮጵያውያን መኪናዎች በቁጣ በተሰባሰቡ የአገሬው ሰዎች ከተሰባበሩ በኋላ በነሱም ላይ ጥቃት ተፈጽሟል። ድረ-ገጹ ጥቃቱን የጥላቻ ጥቃት ብሎታል። ከዚህ ቀደም በደቡብ አፍሪካ በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እስከ ግድያ የደረሰ ጥቃት መሰንዘሩ ይታወቃል።

ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በየሄዱባቸው አንዳንድ አገራት ከአገሬው ህዝብ ከሚደረጉ እንደዚህ ያሉ የጥላቻ ጥቃቶች ባሻገር፣ በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ አገራት የሚሰሩ ሴቶች በአሰሪዎቻቸው አማካኝነት ከፍተኛ የሆነ ጭቆና እንደሚደረግባቸው እና በዛም ምክንያት አንዳንዶች እራሳቸውን እንደሚገድሉ ይታወቃል።

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን በዚህ አመት ባወጣው ሪፖርት ባለፈው የፈረንጆች አመት ብቻ ከ42 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸውን እንዳስታወቀ መዘገባችን ይታወሳል። በኢትዮጵያ የሚካሄደው የመብት ረገጣና አብዛኛውን ህዝብ ከድህነት አረንቋ ለማውጣት ያልቻለው የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ እስካልተለወጠ ድረስም ይህ ቁጥር እንደሚጨምር ይጠበቃል።

## ኢሳትን ከፋሺስታዊ አፈና የመታደግ ግዴታ አለብን!

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንን (ኢሳት) በሚመለከት ሰሞኑ አዲስ አበባን ያዳረሰው ጭውውት የሚከተለውን ይመስላል።

“ዳዊት ጎልያድን ገደለ!”
“በምን?”
“በወንጭፍ!”

“ኢሳት ኢቲቪን ከሳተላይት አወረደ !”
“በምን?”
“ገና ባልታየው ችሎታው”

ይህ ጭውውት እንደ እረኛ ዘፈን ምስጢሮችንና ሕዝባዊ መልዕክቶችን ይዟል።

እርግጥ ነው፤ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ድሮም ቢሆን ዓለም የጉልበተኞች ብቻ አይደለችም። ጎልያድ ተሸንፏል፤ የሮማ ኢምፓየር ወድቋል፤ ስታሊን የገነባት ሶቭየት ኅብረት ፈርሳለች፤ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ኢህድሪ የለችም። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝም ያለ ጥርጥር ይገረሰሳል።

ጥቂት አገር ወዳድ ወጣቶች ወገባቸውን አስረው፤ እንቅልፋቸውን አጥተው ሌት ተቀን በመሥራት በሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞች ያሉት ኢቲቪን ተጋፍጠው ወያኔን አሳበዱት። እስከዛሬ ወያኔ የለመደው ለኢትዮጵያዊያንና ለኢትዮጵያ ወዳጆች የቤት ሥራን መስጠት ነበር። በ97ም ቢሆን የዲሞክራሲ ኃይሎች የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሰጪው ባልጠበቀው መንገድ ሠርተው በመምጣት አደናገጡት እንጂ በዚህ ረገድ የተለየ አልነበረም። ለመጀመሪያ ጊዜ ለወያኔ የቤት ሥራ የሰጠው ኢሳት ነው። ይህም ራስ ምታት ለቀቀበትና ወደ “አጥፍቶ መጥፋት” እንዲያቀና አደረገው።

አዲስ አበቤዎች እንዳሉትም ኢሳት እንደ ቴሌቪዥን አገልግሎት ገና ችሎታው አልታየም። እንደምንገምተው መርሃ-ግብሮቹን ለመተግበር ቀርቶ በቅጡ ለማስተዋወቅ እንኳን ፋታ አላገኘም። ያም ሆኖ ግን ለወያኔ የጣር መንፈስ ሆኖበታል። ኢሳት ከቴሌቪዥን አገልግሎት በላይ ነው። ያለ ወያኔ ፈቃድ ኢትዮጵያዊያን ቤት ውስጥ የገባ አርበኛ ነው። ፌደራል ፓሊስ የሚያስቆመው ነገር አልሆነም። ለወያኔ በኢሳት የሚተላለፈው ነገር ብቻ አይደለም የሚያሳስበው፤ የሚያንገበግበው እሱ የማይቆጣጠረው መሆኑ ነው። ይህ በራሱ ወያኔ “ሁሉ በእጄ፤ ሁሉ በደጄ” እንዳልሆነ አሳባቂ ነው። ስለሆነም በኢሳት ከተላለፈ የተለመደ የፍቅር ዘፈንም ቢሆን ፓለቲካ ነው። ከወያኔ ፈቃድ ውጭ በኢትዮጵያ አየር ናኝቶ ኢትዮጵያዊያን ቤት የደረሰ ከሆነ የተለመደ ዘፈንም ቢሆን ነፃነትን አብሳሪ “ነፃ ዘፈን” ነው። እናም ወያኔ ኢሳትን ለማጣፋት የአሸባሪዎችን ስልት መጠቀሙ የሚጠበቅ ነው። በእውነቱ ሌላ ምርጫም የለውም።

የወያኔ ጭንቀት እየሰጣቸው ባሉት መግለጫዎችም ጭምር እየታየ ነው። ኢቲቪ “ከሳተላይት የወረድኩት አረብ ሳት በደረሰበት የቴክኒክ ችግር ምክንያት ነው፤ እሱም በዚህ አዲስ ቦታ ፈልጉኝ ብሏል” በማለት ከመዋሸት አልፎ የሌላን ድርጅት ስም አጥፍቷል። ይህ ቅሌት የተሞላበት ወንጀል ነው። የመንግሥት ቅጥረኛው ምክትል ዋና ዋሾ ደግሞ “ኢሳት ድሮ ተፈጥሮ የከሰረ ድርጅት ነው፤ አሁንም አድማጭ አጥቶ ከስሯል” ሲል ከመቃዠቱም በላይ “ኢቲቪ ከሳተላይት የወረደው በቴክኒክ ችግር ምክንያት ነው፤ ችግሩን ለመፍታት ከአረብ ሳት ጋር እየሰራን ነው” ሲል ተደምጧል። እነዚህ የመደናበር ውጤቶች ናቸው፤ ገና ከዚህም በላይ መጠበቅ ይኖርብናል።

ወያኔና ነፃ ሚዲያ ዓይንና አፈር ናቸው። ለእውነት የቆመ ነፃ ሚዲያ የወያኔን ዘረኝነት ማጋለጡ አይቀርም። ለእውነት የቆመ ነፃ ሚዲያ የወያኔን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት እና ሥር የሰደደ ክፋትን ማሳየቱ አይቀርም፤ እነዚህም እውነት ናቸውና! ይህ ወያኔን ያስፈራዋል። ከዚህም አልፎ ለእውነት የቆመ ሚዲያ ሕዝብ ከህሊናው ጋር እንዲታረቅ ማድረጉ አይቀርም።

ለእውነት የቆመ ነፃ ሚዲያ ብርሃን ነው። በዚህ ብርሃን ውስጥ “በድብቅ መወየን” አይቻልም። ነፃ ሚዲያ ከጠላት ጋር ያበሩ ባንዳዎችን መደበቂያ ያሳጣል። እናም ወያኔን ብቻውን፤ ራቁቱን እንዲቀር ያደርገዋል። ለዚህም ነው ነፃ ሚዲያ የወያኔ ቀዳሚ የጥቃት ዒላማ የሆነው።

ወያኔ የሚዲያን በተለይም የኢሌክትሮኒክስ ሚዲያን ጉልበት ስለሚያውቅ ነው ሥልጣን ከነጠቀበት እለት ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋቸው። ለይስሙላ ሲል ጥቂት የኤፍ ኤም ሬድዮኖችን ለራሱ ወዳጆች መርጦ ቢሰጥም የኢትዮጵያ ሬድዮ ቅርንጫፎች ሆነዋል።

የኢትዮጵያ ሬድዮኖችና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከተመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ የወቅቱ አምባገነን የሚክቡ፤ የራሳቸው የሚባል ሃሳብ ኖሮዓቸው የማያውቅ ተቋማት ናቸው። በንጉሡ ጊዜ ንጉሡን፤ በደርግ መንግሥቱን፤ በወያኔ ደግሞ መለስን እንዳወደሱ አሉ። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ወገኖቻችን የሚደርስባቸው የህሊና ስቃይ ይሰማናል። ኢሳት ለእነሱም የስቃይ ማስታገሻ ሆኖላቸዋል። ይህም ወያኔን ያስጨንቀዋል።

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሰረበት አንዱ ሰንሰለት ኢሳት በሚባል እሳት እየቀለጠበት ነው። ኢሳት እጅግ ፈታኝ በሆነው የጥቂት ወራት ታሪኩ ውስጥ ሰፊ ድርሳን ሊወጣው የሚችል ትምህርት ሰጥቶናል።

1. የነፃ ሚዲያ ጉልበትን ከንድፈ-ሃሳብ ባሻገር በተግባር አሳይቶናል፤
2. የፀረ-ወያኔ ትግል ዘርፈ ብዙነት በአርዓያነት ገልጦልናል፤
3. በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል የተዘረጋ የሰማይ ላይ ድልድይ ሆኖልናል፤
4. የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ለሚል ሁሉ እድል የሚሰጥ አስታራቂ ተቋም የመሆን ችሎታውን በትንሹም ቢሆን አሳይቶናል፤
5. ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ኢሳት አዝናኝ፣ አንቂ፣ አስተማሪ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝበናል፤

በኢሳት አማካይነት በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጉልበት ምን ያህል እንደሆነ ተገንዝበናል ብለን እናምናለን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ኢሳት መልካም ጅምር መሆኑን ያምናል። ለመሥራቾቹ እና ሌት ተቀን ከሞገድ ጋር እየታገሉ ላሉ ወጣቶች ያለውን አድናቆት ይገልፃል። በዚህ መልካም ጅምር ላይ የወያኔ ፋሺስታዊ ጡጫ ሲያርፍበት ሁላችንም በአንድነት ልንታደገው ይገባል ይላል። ኢሳት የለኮሰው ችቦ እንዲንቦገቦግ ሁላችንም ከጎኑ እንድንቆም ጥሪ ያቀርባል። ኢሳት በአስቸኳይ ወደ አየር ተመልሶ ጠንክሮ እንዲቀጥል ማድረግ እና አሁን በአንድ ቋንቋ የተጀመረው ስርጭትም ደረጃ በደረጃ በሌሎች የአገራችን ቋንቋዎችም እንዲቀጥል ማስቻል የኢትዮጵያዊያን የፓለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ሁሉ የጋራ ኃላፊነት ነው እንላለን። ወያኔን ያርበደበደልንን ተቋም ለማጠናከር እንተባበር።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአምስተርዳም

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከስፍራው ዜናውን አጠናቅሮ የላከልን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ እንደገለጻው፥ በዚህ ወቅት ጣልቃ ገብተው ህይወቱን ያተረፉት ሊያጠቃቸው የመጣው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ጥቃት ሰለባ ስደተኞች እንጂ የተማመነባቸው የደህንነት አጃቢዎቹ አልነበሩም። ተንኳሹ ከአነስተኛ የአካል ጉዳት ጋር ካመለጠ በኋላ ፖሊሶች ይዞ በመመለስ ስደተኞቹን ለማሳሰር ያደረገው ሙከራም እንዳልተሳካለት ለማወቅ ተችሏል።

ስፍራው የተሰበሰቡት ኢትዮጵያውያን፣ በአሉ ይህ ሰው ደረቱ ላይ አስቀምጦት ከመጣው ዘር አጥፊ አምባገነን ሸሽተው በመጡ ስደተኞች የተዘጋጀ እንደሆነ፤ የግለሰቡ ተግባር የሂትለር ፎቶግራፍ ያለበትን ከነቴራ ለብሶ የአይሁዶች ዝግጅት ላይ እንደመገኘት መሆኑን፤ የግለሰቡ አመጣጥ ለመተንኮስ እንደሆነና ለደረሰበት አደጋ ጥፋተኛው እሱ ራሱ መሆኑን ለፖሊሶቹ አስረድተዋል። ለዝግጅት ክፍላችን ከደረሱት ፎቶግራፎች ውስጥ አንዱ ተንኳሹ ጭንቅላቱን በግራ እጁ ላይ አስደግፎ ከፖሊስ መኪና የኋላ ጋቢና ውስጥ ተቀምጦ ከስፍራው ተነድቶ ሲወሰድ ያሳያል።

በበአሉ ላይ ከተገኙት ሰዎች ውስጥ ለዘጋቢያችን አስተያየት የሰጡ ግለሰቦች፥ የመለስ ዜናዊን ምስል የያዘ ከነቴራ ለብሶ መዞር ወያኔ በአፈና በሚገዛባት ኢትዮጵያ ይቻል ይሆናል እንጂ፤ በነፃ አገራት በሚኖረውና በአብዛኛው የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ በሚቃወመው የውጭ አገር ኢትዮጵያዊ ዘንድ የማይታሰብ ነው።

በአሜሪካ ዋና ከተማ የሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ በቅርቡ ባከናወነው ጥናት መሰረት፥ በዋሽንግተን ዲሲ ከሚገኘውና ቁጥሩ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ መሃል 95 ከመቶ የሚሆነው የዘረኛው ስርአት ተቃዋሚ መሆኑን እንዳረጋገጠ ለወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባቀረበው ዘገባ አስታውቋል።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002 (ክፍል 5 የመጨረሻ ክፍል)

- **የ2002 ምርጫ ህዝብ በ1997 ምርጫ በብዙ መስዋእትነት ሰለ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ምንነት የተማረውን ትምህርት ትክክለኛነት ዳግም አረጋግጦለታል። ስልጣን ከሃቀኛ የዲሞክራሲ ሂደት ውጭ በአዝጋሚም መንገድ ሆነ በአቋራጭ መያዝ እንደማይቻል ግልጽ አድርጎልናል።** የምርጫ ሰነድ አዝጋጅቶ "ከሌላው ድርጅት በእነዚህ ፖሊሲዎቼ እለያለሁ ምረጡኝ" ለማለት ከመዘጋጀት በፊት የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ጠንቅ የሆነውን ወያኔን ከስልጣን ማባረር ግዴታችን መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ከዚህ ቀደም መሬት በግል ንብረትነት የሚያዘው በኢህአዴግ መቃብር ላይ እንዳለው ሁሉ ስልጣንም በምርጫ በዴሞክራሲ ስም ከወያኔ መውሰድ የሚቻለው በወያኔ መቃብር ላይ መሆኑን ግልጽ አድርጎልናል። **ትግሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር በሆነ የምርጫ ቦርድ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የፍትህ ሥርዓት፣ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል ምርጫ ተካሂዶ እንዴት ስልጣን እንይዛለን ሳይሆን እነዚህ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ ሆነው ተደራጅተው እንዴትስ ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች በእኩልነት እንዲያገለግሉ ማድረግ ይቻላል የሚል ብቻ እንደሆነ የማያሻማ ሆኗል።**
- እነዚህ ምክንያቶች ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማኅበራት እና የሃገሪቱ ሕዝብ በጋራ እውነተኛ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲጀመር በቅድሚያ ተባብረው ሊሰሩት የሚገባ፣ በመካከላቸው የሚኖሩ ማናቸውም ልዩነቶች፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የውጭ ጉዳይ የፖሊሲ ልዩነቶች በምንም አይነት ሊያደናቅፉት የማይገባ የጋራ ዓላማ ያላቸው መሆኑን አሳይተዋል። ይህ የጋራ ዓላማ አገራችን በአጭር የሽግግር ሂደት አልፋ ከአምባገነንነት በሕዝብ ነፃ ምርጫ ላይ ወደ ተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ ሥርዓት መሸጋገር እንደሚኖርባት ነው። ለዚህም ሽግግር መሳካትና ተጠናክሮ መቀጠል የዴሞክራሲ ምርጫና መንግሥታዊ ሥርዓት ዋልታ የሆኑትን ነፃ ማኅበረሰባዊና መንግስታዊ ተቋማት መገንባት የሽግግሩ ወቅት ተቀዳሚ ሥራ መሆን እንደሚገባው ነው። ባለንበት ዘመን ከወያኔና የትግላችው ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰለሚመጣ ለውጥ ቁብ ከማይሰጡ ጥቂት ድርጅቶች በስተቀር ከዚህ በላይ በተቀመጠው ጥቅል የጋራ ዓላማ የማይስማማ አይኖርም። ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ወደ ተባለው ግብ በጋራ ተነስተን እንዴት በጋራ እንደርሳለን የሚለው ብቻ ነው።

## 6.5 ከጋራ ፍላጎት ወደ ጋራ ዓላማ፤ ከጋራ ዓላማ ወደ ጋራ ትግልና ድል እንዴት?

6.5.1 ለጋራ ትግልና ድል መሠረት የሚጣለው በድርጅቶች መካከል ኅብረት ለመፍጠር የሚደረገውን በጥንቃቄ በመከነወን ሂደት ነው ። ከላይ በ 6.2 የቀረበውን ማሳሰቢያ በጥሞና ማጤን ጠቃሚ ነው።

6.5.2 በድርጅቶች መካከል በተደረጉ ውይይቶች የታየውን ተባብሮ የመሥራት ፍላጎት ዘላቂ እንዲሆን ለመሥራት ፍላጎቱ ያላቸው ድርጅቶች፣ ለራሳቸውም ሆነ በጉጉት ለሚጠብቃቸው ሕዝብ ከየት ተነስተው በምን አቋርጠው የት እንደሚደረሱ በግልጽና በያሻማ ቋንቋ የተቀመጠ የተሟላ እቅድ ( road map ) ሊኖራቸው ይገባል። ይህ የተሟላ እቅድ ድርጅቶቹ እርስ በርስ ቃል ኪዳን የሚገቡበት ብቻ ሳይሆን ለሕዝብም ጭምር ቃል የሚገቡበት መታሰሪያቸው ይሆናል። በዚህ እቅድ ውስጥ በሚካተቱ መሠረታዊ ነጥቦች ላይ አንድ ወጥ የጋራ ስምምነት ሳይደረስ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሆነ ወይም "ለጥቂት ጊዜ አብረን መስራት እስከቻልን ሌላውን ችግር ጊዜ ይፈታዋል" በሚል የሚደረግ ውለታና ስምምነት ከቶውኑ ሊኖር አይገባም። በተውሸለሸለ መንገድ በሚፈጠር ትብብር የሕዝብ ቅስም በድጋሚ እንዲሰብር ልንፈቅድ አይገባም። በአገራችን ድርጅቶች መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል የሚያፀናው

1. **የድርጅቶችና የመሪዎቻቸው ቀና ፍላጎትና አርቆ አሳቢነት፤**
2. **በተወሰን ደረጃም ቢሆን በሕዝብ ፊት የተገባ ቃል ኪዳንና፤**
3. **ውሉን በሂደት ለማፍረስ ሰበብ ሊሆኑ ይቻላሉ ተብለው የሚታሰቡ ማናቸውም ችግሮች አስቀድሞ የታሰበባቸውና መፍትሄ የተሰጣቸው ከሆኑ ብቻ ነው።** በመሆኑም የተባለው እቅድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ያካተተ ሊሆን ይገባዋል።

1. ሁሉም ድርጅቶች የሚተባበሩበተን የጋራ ምክንያትና ግብ፣ በጋራ የሚጋሩዋቸውንና በምንም አይነት ሁኔታ የማይጥሷቸውን መሠረታዊ የጋራ እሴቶች የሚያሳይ ሰነድ
2. የጋራ ትግሉ የሚያልፍባቸውን ዋና ምዕራፎችና በየምዕራፉ የሚሠሩ ሥራዎችን በዝርዝር የሚያሳይ ሰነድ፣ ለምሳሌ
   - የትግል ምዕራፎቹ ምን እንደሚሆኑና በየምዕራፉ ስለሚከናወኑ ተግባራት፣
   - ወያኔ ከስልጣን ተወግዶ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚሰይም መንግስት እስከሚሰየም ድረስ የሚኖረው የሽግግር ሂደት ምን ይመስላል? እንዴት ይዋቀራል፣ ምን ተግባራት ይኖሩታል?
   - ለዴሞክራሲ ሥርዓት ዋስትና ይሆናሉ ተብሎ የሚታሰቡትና በሽግግር ወቅት ይቋቋማሉ የተባሉት ተቋማት በተባባሪዎቹ ውልና ፍላጎት መሠረት እንዴት ነፃና ገለልተኛ ሆነው በሁሉም የተብብሩ አካላት ተቀባይነት እንዲያገኙ ተደርገው መዋቀር ይቻላሉ? የዚህ ሥራ ኃላፊ እንዲሆን ማንን በጋራ ተስማምተው ይሰይሟሉ? ይህ አካል የሚሰጠውን ውሳኔ በጸጋ ለመቀበል አስቀድመው መስማማታቸውን የሚያሳዩ ሰነዶችን ማን ያዘጋጃል፤ ማንስ ያስፈጽማቸዋል?
3. የጋራ ዓላማቸውን ለማሳካት ተባባሪዎቹ የሚጠቀሙበትንና ሥራን ስሉጥ በሆነ መንገድ የሚያሠራ የተብብሩ ድርጅታዊ መዋቅር ምን መሆን ይገባዋል? ትብብሩ ምን አይነትስ ህገ-ደንብ ይኖረዋል?

እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ካሁኑ ምላሽ ይፈልጋሉ። እነዚህና ሌሎችም መሠረታዊ ሰነዶች በዝርዝር ተዘጋጅተው የትብብሩ ስምምነት ወይም ውል አካል መሆን አለባቸው። በትብብሩ የጋራ ጉዞ የድርጅት ወይም የመሪዎች ጠባብ ፍላጎቶች ሊያደፈሩሱዋቸው ብሎም ትብብሩን ሊያመክኑ የሚችሉ መሠረታዊ ጉዳዮች በይደር መታለፍ አይኖርባቸውም። መሠረታዊ የሆኑ ሰነዶች አስቅድመው ገና የትብብሩ ውል በድርጅቶች መካከል ከመፈረሙ በፊት የሚጠናቀቁ በመሆናቸው፣ የሰጥቶ መቀበል የድርድር ውጤት እንጂ ድርጅቶች በመቧደን ወይም በትብብሩ ውስጥ በሚኖራቸው ወንበሮች ቁጥር የሚወሰኑ አይሆንም።

በመሆኑም የወደፊቱ ሥራ ይህ በሙሉ ስምምነት ተቀባይነት ያገኘን ዝርዝር እቅድ (road map) በተግባር ለመተርጎም ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውጭ ድርጅቶችን ሊያጨቃጭቁ የሚችሉ የውሳኔ ጉዳዮች አይኖሩም። ይህ አሠራር ድርጅቶች ብዙ ወንበር ስላላቸው ወይም በፖለቲካ ዓላማቸው ስለሚቀራረቡ አንዱ በሌላው ኪሳራ የሚፈልገውን በማስወሰን ችግር ይፈጥርብኛል የሚል ስጋትና ጥርጣሬን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። በትብብሩ የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ በመቀመጥ ሊገኝ የሚችልን ጠቀሜታ ስለሚያሳንሰው ከየድርጅቶቹ የሚነሳውን የስልጣን ሽኩቻ ይቀንሰዋል። የትብበሩ አካላት ቁጥር ቢበዛ የሚያሰበረግግ አይሆንም። እንዲያውም በርካታ ቡድኖች የትብብሩ አካል እንዲሆኑ፣ ብዙሃኑን ያካተተ፣ ማናቸውም ፈተናዎች የማያኮላሹት ጠንካራ ትብብር እንዲኖር የሚያበረታታ ይሆናል።

በመጨረሻም በአገራችን እውነተኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲመሰረት በጋራ ለመሥራት በሚደራደሩ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ ድርድር በንግድ ባላንጣዎች መካከል የተፈጠረን ቅራኔ፣ ወይንም ኑዛዜ ባልተገኘለት ወራሾች መካከል የሚደረግ ድርድር ተደርጎ መታየት የለበትም። በእነዚህ ድርድሮች እያንዳንዱ አካል የተቻለውንና ያህል ተጠቃሚ የሚያደርገውን ድል ለመቀዳጀት ተግቶ ይሰራል። አንዱ ሌላው የሚፈልገውን እንዳያውቅ የመደራደሪያ ካርዶቹን ማንም እንዳያይበት ደረቱ ላይ ለጥፎ ይቀመጣል። አንዱ ሌላውን አካል የሚያቀርበውን መደራደሪያ በንፉግ መንፈስ ተሸፋፍኖ ያየዋል። በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱት አካላት በድርድር ችግራቸውን መፍታት ካልቻሉ ጉዳያቸው ወደ ህግና ዳኝነት ሄዶ መፍትሄ ያገኛል የሚል እምነት ስላላቸው በድርድር አንድ አይነት ስምምነት ላይ ካልደረሱ የድርድሩን መቋረጥ የሞትና የሽረት ጉዳይ አድርገው አያዩትም።

በአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ ድርድር ከላይ በጠቀስናቸው ምሳሌዎች መንፈስ ሊከናወን አይችልም። **ድርድሩ ሁሉንም አሸናፊና ተጠቃሚ አድርጎ ሊያወጣ በሚችል መርህ ብቻ ነው ሊመራ የሚችለው።** የድርድር ሂደት ቢደናቀፍ ከጋራ ውድመት በስተቀር በገላጋይ የሚተርፈን ጠቀሜታ አይኖርም። "ድርጅቴ ምን ያገኛል? እኔ ምን እጠቀማለሁ?" ከሚል ስሌት በላይ ተሻግሮ ሁላችንም **"የዛች መከረኛ አገር ሕዝብ ምን ያገኛል? የመተባበሩን ሥራ እንዲሰምር ድርጅቶች እንዲቀራረቡ ድርጅታችን ምን ማዋጣት ይችላል?"** በሚል ቀና መንፈስ የምንቀርበው ብቻ ነው መሆን የሚችለው። አንዳችን በሌላው ኪሳራ ትርፍ የምናገኝበትን ስሌት አስልተን ወደ ትብብር ምሥረታ የምንጠጋ ከሆነ እንኳን የትብብሩን ዓላማ ልንመታ ይቅርና ትብብሩም በእግሩ እንኳን ማቆም እንደማንችል መታወቅ ይኖርበታል።

ይህንን ሃቅ ከምር በመረዳት የግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አገራዊና ሕዝባዊ ለሆነውን የመተባበር ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተቀመጡትን እና ከሌሎች ወገኖቻችን ጋር በሚደረጉ ምክክሮች የሚታከሉ ቁምነገሮችን የመተባበሪያችንን መሠረት አድርገን ከተነሳን የተዋጣለት ትብብር በማድረግ የወያኔን ዘረኛና አምባገነናዊ ሥርዓት እድሜ እናሳጥራለን። (ተፈጸመ)

## በአዲስ አበባ ከተማ በደረሰ የመኪና አደጋ ከ26 በላይ ሰዎች መሞታቸው

ቅዳሜ ሃምሌ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በደረሰ የመኪና አደጋ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ሃያ ስድስት ሰዎች ሞተው በርካቶች መቁሰላቸው ተዘግቧል።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ፣ በተለምዶ 18ኛው ማዞሪያ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ አንድ የጭነት መኪና እና መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶቢስ ከጠዋቱ አራት ሰአት ተኩል ላይ ሲጋጩ የደረሰው አደጋ የበርካቶችን ህይወት መቅጠፉን ሪፖርተር ጋዜጣ ዘግቧል።

የጭነት መኪናው ከመለስተኛ አውቶቢሱ ጋር ከመጋጨቱ በፊት በመንገደኞች ላይ ጉዳት ማድረሱን እና አምስት ሰዎች መግደሉም ታውቋል። ይህም የመኪናው ፍሬን ሳይበጠስ እንዳልቀረ ጥርጣሬን ፈጥሯል።

## ታቦ ኢምቤኪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያደረጉት ንግግር በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መሪዎች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ መሰንበቱ ታወቀ

የቀደሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት እና እውቁ የጸረ-ዘረኛነት የነጻነት ታጋይ ታቦ ኢምቤኪ ባለፈው ሳምንት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክተሬት በተቀበሉበት ክብረ በአል ላይ ያደረጉት ንግግር አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል።

ባለፈው ቅዳሜ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ባዘጋጀው የተማሪዎች ማስመረቂያ በአል ላይ በመገኘት የክብር ዶክተሬት ዲግሪያቸውን የተቀበሉት ፕሬዚደንት ኢምቤኪ ያደረጉት ንግግር ሙሉ በሙሉ ያተኮረው በተለይ ለደቡብ አፍሪካውያን፤ እንዲሁም ለአፍሪካውያን በሙሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚሉት ቃላቶች ያላቸውን ክብር እና ከፍተኛ ቦታ በመግለጽ ላይ ነበር።

ፕሬዚደንት ኢምቤኪ በንግግራቸው፥ "ኢትዮጵያዊነት የአፍሪካ ብሄረተኛነት መሰባሰቢያ ነው። መላው አፍሪካ ነጻነቱን በቅኝ ገዥዎች ተገፎ በኖረበት ዘመን ኢትዮጵያውያን ነጻነታቸውን አስከብረው መገኘታቸው፤ ነጻነታቸውን ሊቀማ የመጣ ወራሪ አድዋ ላይ ድል መተው አሳፍረው መመለሳቸው፣ የአፍሪካውያን ምሁራንና የነጻነት ታጋዮች የይቻላል እምነት መሰረት ነበሩ። የሞራል ብርታት፣ የተስፋ ምንጭ ነበሩ።" ብለዋል። ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክና ገናና ስልጣኔ ያላት ሃገር በመሆኗ የአፍሪካውያን ኩራትና በራስ የመተማመን ምንጭ መሆኗን ፕሬዚደንቱ ግልጸዋል።

ከታቦ ኢምቤኪ ንግግር መሃል አነጋጋሪ ሆኖ የሰነበተው ጉዳይ ግን ፕሬዚደንቱ ኢትዮጵያን እንደ አፍሪካ ህዝብ አንድነት ምሰሶ ቀርጸው ያቀረቡት ሰፊ ሃተታ ነው። እንደሳቸው ንግግር ኢትዮጵያና ነጻነት፤ እንዲሁም ኢትዮጵያና አፍሪካዊ ኩራት ተወራራሽ ቃላት ናቸው። ይህም በባህል እና በቋንቋ ውጥንቅጡ የወጣውን አፍሪካ አንድ ሆኖ እንዲቆም ለማድረግ ያስቻለ ቃልና ጽንጸ ሃሳብ ነው። በዩንቨርሲቲው ውስጥ ያሉ ምንጮቻችን እንደገለጹልን የኢምቤኪ ንግግር በወያኔ ባለስልጣናትና የወያኔ አገልጋይ በሆነው የዩንቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አልተወደደም። "ልንሸልመው ጠርተነው ሰድቦን ሄደ" አይነት የባለስልጣናት አስተያየቶችም ተደምጠዋል።

በተለይ አንድ የዩኒቨርሲቲው ምንጫችን እንደገለጹት፥ የፕሬዚደንቱ ንግግር ኢትዮጵያዊነትን በማራከስ በኢትዮጵያዊነት ሃገራዊ ስሜት ዙሪያ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይሰባሰብ የዘር ፖለቲካን የኢትዮጵያዊነት መምቻ አደርጎ የሚጠቀም ዘረኛና ከፋፋይ የሆነ የወያኔ አገዛዝ ላይ የተሰነዘረ ቀጥተኛ ጥቃት አስመስሎባቸዋል። በዚህ ሰሞን የታቦ ኢምቤኪ ንግግር መነጋገሪያ ላጣው የዩንቨርስቲ ማህበረሰብ ዋና የመነጋገሪያ ርእስ ሆኖ መሰንበቱንም ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።

### የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከፍተኛ ትርፋማነት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ተቋሙን ከፍ ወዳለ ስኬት በመውሰድ የሚታወቁት ስራ አስኪያጁ አቶ ግርማ ዋቄ ባለፈው አመት በፓርላማ የመሰረተ ልማት ጉዳዮች ኮሚቴ ፊት ቀርበው እንዳስረዱት፣ ድርጅቱ ብቃትን ወደ ጎን በመተው በዘር ላይ የተመሰረተ ቅጥር እንዲፈጽም ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ጫና እያደረገ ነው። አዲስ ፎርቹን የተባለው ሳምንታዊ ጋዜጣ በወቅቱ እንደዘገበው፥ አቶ ግርማ ዋቄ በዚህ ጫና ምክንያት ከሆነ ዘውጌ ማህበረሰብ የሆኑ ሰዎችን ለስራው ብቃት ሳይኖራቸው እንዲቀጥሩ መገደዳቸውን ገልጸዋል። እንዲህ አይነቱ አሰራር ከቀጠለም ድርጅቱ ለውድቀት እንደሚዳረግ እና ከስራ ውጪ እስከመሆን ሊደርስ እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

ለዝግጅት ክፍላችን የኢ-ሜይል መልክት የላኩት ግለሰብ፣ አቶ ግርማ ዋቄ የተናገሩት ነገር በየቦታው እራሱን ማሳየት የጀመረ መሆኑን ገልጸው፣ የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ አሰራሩን በሁሉም መንግስታዊ ተቋማት ላይ ለማስፈን ካለው ፍላጎት የተነሳ ይህንን ኩሩ ድርጅትም ያፈራርሰዋል በሚል እንደሚሰጉ ጽፈዋል።

### የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጠና የፈጠረው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዩኒቨርሲቲዎች እንዲያስተምሩ የታጩ ሲሆን፤ ከመጪው ሙያቸው ጋር የተያያዘ ስልጠናን በመስጠት ስም በአዳማ እና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲዎች ተሰብስበው ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲሰበኩ ሰንብተዋል። ዘጋቢያችን ያናገራቸው ተሳታፊዎች፣ "ድብርቱ ሊገለን ነው፤ የስብከቱ አድካሚነት ብቻ ሳይሆን የሰንበት እረፍት እንኳ አይሰጡንም" ብለውታል።

ከዚህ ቀደም እንደተካሄዱት ስልተናዎች ሁሉ ይሄኛውም በህዝብ ገንዘብ እየተካሄደ እንዳለ ሪፖርተራችን በዘገባው አክሏል።

## የአሜሪካ መንግስት በሙስና የተዘፈቁ አፍሪካውያን መሪዎችን ገንዘብ በቁጥጥር ስር አውላለሁ አለ

አሜሪካ ከዚህ በኋላ በሙስና በተዘፈቁ መሪዎቻቸው አማካኝነት ከአፍሪካውያን ለተሰረቀ ገንዘብ ማከማቻነት አታገለግልም ሲሉ የኦባማ አስተዳደር የፍትህ ቢሮ ሃላፊ አቶ ኤሪክ ሆልደር መናገራቸውን የዩጋንዳው ደይሊ ሞኒተር ዘግቧል።

ባለፈው ሳምንት በዩጋንዳ በተካሄደው የአፍሪካ አንድነት ጉባኤ ላይ ለአገራቱ መሪዎች ራሳቸው ባደረጉት ንግግር፣ የአሜሪካ መንግስት ከአፍሪካ ተሰርቆ በምእራባውያን አገራት ባንኮች ተደብቆ ያለን ገንዘብ መያዝ እንደሚጀምር አሳውቀዋል። አቶ ኤሪክ ሆልደር በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሮ እየተከታተለ የሚያስፈጽም የጠበቆች ቡድን ማቋቋማቸውንም እንዳበሰሩም ዘገባው ገልጿል። በጉዳዩ ላይ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡ ግለሰብ፥ "ይህ ቃል በስራ መተርጎም ቢጀምር መጀመሪያ የሚያዘው የኛዎቹ ጉደኞች ገንዘብ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ" ብለዋል። የወያኔ መሪዎች ለረዥም አመታት የህዝብ ገንዘብ እየሰረቁ ወደ ውጭ አገራት ሲልኩ እንደቆዩ በተለያዩ አካላት ክስ እንደሚቀርብባቸው የሚታወቅ ሲሆን፤ ከጥቂት ወራት በፊት ለግንቦት 7 ሬድዮ ቃለ መጠይቅ የሰጡት የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት መሪ ዶ/ር ግሬጎሪ ስታንተን፣ ከተለያዩ ተአማኒ ምንጮች ባሰባሰቡት መረጃ መሰረት መለስ ዜናዊ በቢሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ በውጭ ባንክ አስቀምጧል ብለው እንደሚያምኑ መግለፃቸው ይታወሳል።

## የወያኔ አገዛዝ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የሚፈጽመው ኢ-ሰብአዊ እርምጃ ሳይገታ ቀጥሏል፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ሊፈናቀሉ ነው

በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ለከተማ ልማት በሚል እንደሚፈናቀሉ የተነገራቸው በርካታ ነዋሪዎች ያለመድረሻ እንደቀሩ ለግንቦት 7 ድምጽ የአዲስ አበባ ዘጋቢ ስሞታቸውን ገልጸዋል።

215 የሚሆኑት ዜጎች የሚፈናቀሉበት ምክንያት መኖሪያዎቻቸው ባሉበት ቦታ ኮንዶሚኒየሞች እንዲሰሩ ስለታቀደ ነው። ምንም እንኳ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን ተፈናቃዮቹ ከፍተኛ ካሳ እንደተሰጣቸው ቢናገሩም፣ ከዚህ ቀደም ከልደታ አካባቢ የተፈናቀሉ ዜጎች ለጋዜጠኞችን እንደተናገሩት፣ የሚሰጣቸው ገንዘብ የቤት ኪራይ ዋጋ ለአዲስ ቤት ፈላጊዎች ከፍተኛ መሆኑን ከግምት ውስጥ ያላስገባ እና እዚህ ግባ የማይባል ነው።

ከከፍያው ማነስ በተጨማሪ፣ በተፈናቃዮቹ ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ የቆየው ጉዳይ የሚፈናቀሉት ለከተማዋ እድገት ሳይሆን ለካድሬዎች መኖሪያ ለማመቻቸት ነው ብለው ማመናቸው ነው። ከዚህ ቀደም በከተማይቱ ከተሰሩት ኮንዶሚኒየሞች ውስጥ በአንዳንዶች ግምት ወደ 80% የሚሆነው የተሰጠው ለአገዛዙ ካድሬዎች፣ የፓርቲ አባላት እና ደጋፊዎች እንደሆነ ይነገራል።

ዴሞክራሲያዊ በሆኑና ባደጉ አገሮች ለአንድ ማህበረሰብ የበለጠ ጥቅም ያበረክታል ተብሎ የተገመተ የመንግስት ስራ ሲሰራ የሚፈናቀሉ ሰዎች ካሉ፤ ቀድሞ ለነበራቸው ንብረት ከእጥፍ ድርብ በላይ ካሳ እንደሚከፈል ይታወቃል። ለባለ ንብረቶች ብቻ ሳይሆን ቤት ተከራዮች እንኳ በመንግስት የግንባታ እቅድ ምክንያት እንዲፈናቀሉ ከተደረገ፣ አዲስ ቤት ለመፈለጊያ፣ ለመጓጓዣ እና ለበርካታ ወራት የሚሆን ኪራይ ክፍያ በካሳ መልክ መስጠት እንደ አሜሪካን ባሉ አገሮች የተለመደ ተግባር ነው።

በኢትዮጵያ፣ በተለይም በአዲስ አበባ፣ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ዜጎችን ያለ ካሳ በጭካኔ እንደሚያፈናቅል ይታወቃል። የዛሬ ሁለት ወር አካባቢ በአዲስ አበባ ከሁለት ሺህ በላይ የቀበሌ እና የኪራይ ቤቶች ተከራይተው ይኖሩ የነበሩ ከሁለት ሺህ በላይ ዜጎች ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እንዲፈናቀሉ ተደርጎ፣ ምትክ መኖሪያ ለማግኘት ከአስር እስከ ሃያ ሺህ ብር በነፍስ ወከፍ መጠየቃቸውን ኢትዮጵያ ዛሬ የሚባለው ድረ-ገጽ መዘገቡን መጥቀሳችን ይታወሳል።

### ወያኔ የኢትዮጵያን የደን ሽፋን በሶስት እጥፍ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሚደነገው ቁጥር በጣም አነስተኛ እንደሆነ እና ባጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ ያለው ሁኔታ የደን መጨፍጨፍ እንጂ ማደግ እንዳልሆነ አስረድተዋል።

የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ የፈጠረውን አሉታዊ ሁኔታ ለመሸፈን አዎንታዊ ዜና የመፈብረክ ፖሊሲን የሚከተል ሲሆን፤ ይህንንም ለማስረገጥ የተለያዩ መሻሻሎች እንደተከሰቱ የሚያሳዩ ቁጥሮችን እንደሚያመርት ይታወቃል። ከጥቂት ወራት በፊት ኢትዮጵያን በሚመለከት ጽሁፍ ያቀረቡት ሄለን ኤፕስቴን የተባሉ አሜሪካዊት ተመራማሪ፥ የወያኔ አገዛዝ ክትባት ስለተቀበሉ ህፃናት እና የወሊድ መቆጣጠሪያ ስለሚጠቀሙ ሴቶች ቁጥር ሳይቀር እንደሚያሽ መጥቀሳቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org